**የቨርጂኒያ COMMONWEALTH DEPARTMENT FOR AGING AND REHABILITATIVE SERVICES (የእርጅና እና መልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች መምሪያ) የአዋቂዎች ጥበቃ አገልግሎት ክፍል**

| **ለቢሮ አጠቃቀም ብቻ፡-** ማመልከቻውን የተቀበሉበት ቀን |
|---|
| LDSS |
| የጉዳይ# |

# ለአዋቂዎች አገልግሎት የሚቀርብ ማመልከቻ

| | |
|---|---|
| ስም፡- | የትውልድ ቀን (ወር/ቀን/ዓመት)፡- |
| የመንገድ አድራሻ፡- | |
| ከተማ፣ ግዛት፣ ዚፕ፡- | ስልክ ቁጥር፡- |
| የመልዕክት አድራሻ (የተለየ ከሆነ)፡- | |
| ወደ ቤት የሚወስደው መንገድ አቅጣጫ (አስፈላጊ ከሆነ) | |

**ለሚከተሉት አገልግሎት ወይም አገልግሎቶች አመልካች ነኝ (ሁሉንም ይዘርዝሩ)፡-**

☐ መብቶቼ እና ኃላፊነቶቼ ተገልጸዋል እንዲሁም በጽሑፍ የሰፈረውን ቅጂ ተቀብያለሁ።

☐ የምሰጠው መረጃ ትክክል መሆኑን አረጋግጣለሁ። የተሳሳተ መረጃ ከሰጠሁ በሕግ ልከሰስ እንደምችል እገነዘባለሁ።

☐ የአካባቢው መምሪያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግለሰቦች ወይም ኤጀንሲዎች እንዲያነጋግር ፍቃድ እሰጣለሁ። ያለዚህ የአካባቢው መምሪያ ብቁነቴን መወሰን ላይችል እንደሚችል ተረድቻለሁ።

| ሰው/ኤጀንሲ | ምክንያት | የደንበኛው የመጀመሪያ ስም | ቀን |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

የአመልካቹ ፊርማ ቀን

በምልክት ወይም በጣት አሻራ የተፈረመ ከሆነ ለዚህ ወኪል ወይም ምስክር

**ተሞልተው የተጠናቀቁ ማመልከቻዎች አዋቂው በሚኖርበት አካባቢ ወደሚገኘው ማህበራዊ አገልግሎት መምሪያ መላክ አለባቸው።**

**የአካባቢዎን መምሪያ ለማግኘት www.dss.virginia.gov/localagency/index.cgi ን ይጐብኙ።**

## **የአመልካቾች መብቶች**

ማንኛውም ሰው አገልግሎት ለማግኘት ማመልከት ይችላል። በካውንቲው ወይም በከተማው ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ መቆየት አያስፈልግዎትም። ለአገልግሎቶች የዜግነት መስፈርቶች የሉም።

በዘር፣ በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በዜግነት ወይም በአካል ጉዳት ሳይለዩ እኩል የመስተናገድ መብት አለዎት።

አገልግሎቶችን በሚጠይቁበት ቀን ማመልከቻ የማግኘት እና ሞልተው የማጠናቀቅ መብት አለዎት። ማመልከቻውን ለመሙላት እገዛ ከፈለጉ አንድ ሰው ይረዳዎታል።

ብቁነትን የመወሰን ሂደት ለእርስዎ ሊብራራ ይገባል።

የአካባቢው መምሪያ ማመልከቻዎን በተመለከተ በ45 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ያስተላልፋል። ይህ የማይቻል ከሆነ ለምን እንደሆነ ሊነገርዎት ይገባል። የአካባቢው መምሪያ ብቁ ካልሆኑ ወይም መዘግየት ካለበት ለእርስዎ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት።

ብቁ እንደሆኑ ከተረጋገጠ፣ የአካባቢው መምሪያ ማመልከቻዎን ከተቀበለ በኋላ በ45 ቀናት ውስጥ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አለዎት።

ብቁ ለመሆን የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን የሚያሟሉባቸው በመንግስት መቅረብ ያለባቸው አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለዎት። አማራጭ አገልግሎት የማግኘት መብትዎ የሚወሰነው የብቁነት መስፈርቶችን በማሟላትዎ ላይ እና የአከባቢው መምሪያ አገልግሎቱን የሚሰጥ ወይም የማይሰጥ በመሆኑ ላይ ነው።

በአካባቢው መምሪያ በአገልግሎት መዝገብ ውስጥ ስላለው እርስዎን የተመለከተ መረጃ የማየት መብት አለዎት።

የአካባቢው መምሪያ ከማህበራዊ አገልግሎት ፕሮግራሞች አስተዳደር ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ዓላማዎች ካልሆነ በስተቀር ያለእርስዎ የጽሑፍ ስምምነት ስለእርስዎ መረጃ ሊሰጥ አይችልም።

እነዚህ መብቶች በፌዴራል እና በግዛት ህጎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው ነገር ግን የተወሰኑ ልዩነቶች አሉ። ጥያቄ ካለዎት ወይም በመዝገብዎ ውስጥ ያለውን መረጃ ማየት ከፈለጉ እባክዎ ሰራተኛዎን ያነጋግሩ።

## **የይግባኝ መመሪያ**

የቨርጂኒያ ኮድ ክፍል 51.5-147 በቤት ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን (**የቤት እመቤት፣ የቤት ሥራ ወይም ጓደኛ**) እና **የአዋቂ አሳዳጊ እንክብካቤ አገልግሎቶችን** የሚያመለክቱ ወይም የሚቀበሉ አመልካቾች የአከባቢ ቦርድ አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ ለመከልከል፣ ለመቀየር ወይም ለማቋረጥ ማንኛውንም ውሳኔ ይግባኝ እንዲሉ ይፈቅድላቸዋል። ማንኛውም አመልካች ወይም አገልግሎት የሚቀርብለት ሰው የአካባቢው ቦርድ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ አለመስጠቱን በተመለከተ በኮሚሽነሩ ግምገማ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላል።

በአካባቢው መምሪያ ውሳኔ ካልተደሰቱ ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ይህንን ማድረግ ያለብዎት የድርጊት ማስታወቂያ ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ከ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። በቀጥታ በመጻፍ ወይም ይግባኙን በፋክስ በመላክ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ፦


ትኩረት፦ ቁጥጥር<br>
Virginia Department for Aging and Rehabilitative Services (የቨርጂኒያ የእርጅና እና መልሶ ማቋቋም አገልግሎቶች መምሪያ)<br>
9960 Mayland Drive፣ Suite 200<br>
Richmond፣ Virginia 23233<br>
804-527-4524 (ፋክስ)


**ይግባኝ ለመጠየቅ በሚቀርበው ጥያቄ ላይ የሚከተለው መረጃ መታየት አለበት፦ "የጉዳይ ኮድ 35" እና "የጉዳይ ዓይነት APA።"**

በ10 ቀናት ውስጥ ችሎት እንዲጠራ ከጠየቁ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ አገልግሎትዎ ወይም የአገልግሎት ክፍያዎ ይቀጥላል።

በማንኛውም ጊዜ አድልዎ እንደተደረገብዎት ከተሰማዎት Commissioner of the Department of Social Services (ለኮሚሽነሩ ማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ) ወይም U.S Department of Health and Human Services (ለዩናይትድ ስቴትስ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ)፣ የሲቪል መብቶች ቢሮ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። ይህ የሚደረገው አድልዎ ድርጊት ተፈጽሞበታል ከተባለበት ቀን በ 180 ቀናት ውስጥ መሆን አለበት። ተጨማሪ መረጃ በ http://www.dss.virginia.gov/about/civil_rights/index.cgi ላይ ይገኛል

## **የአመልካቾች ኃላፊነት**

ብቁነትዎን ለመወሰን የሚያስፈልጉትን የተሟላ እና ትክክለኛ መረጃዎችን መስጠት አለብዎት። የአከባቢው መምሪያ የደመወዝ ክፍያዎችን ወይም ሌሎች ዓይነት ሰነዶችን ወይም የገቢዎን ማረጋገጫ ለማግኘት ኤጀንሲዎችን ወይም ግለሰቦችን ለማነጋገር ፈቃድ ሊጠይቅዎት ይችላል። የተሳሳተ መረጃ የሚሰጡ ከሆነ በሕግ ሊጠየቁ ይችላሉ።

ለአገልግሎት ብቁነትዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ማናቸውንም ለውጦች በ 10 ቀናት ውስጥ ለአከባቢው መምሪያ ማሳወቅ አለብዎት።